# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ.** 239626

ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኘ

**አመልካች** - አቶ ብርሃኑ አደራ - አልቀረቡም

2. አቶ ኃይሉ አደራ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች** - 1. ወ/ሮ ብርቄ አደራ

3.ወ/ሮ ደስታ አደራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በቡራዩ ከተማ ገፈርሳ ጉጄ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ የእናታችን የውርስ ይዞታና ንብረት አመልካችን ጨምሮ በሌሎች የስር ተከሳሾች እጅ ስለሚገኝ ድርሻችንን እንዲያካፍሉን በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የስር ተከሳሾች በጋራ በመሆን የተለያዩ መቃወሚያዎችን በማስቀደም በሰጡት መልስ በክሱ በተራ ቁጥር 1ኛ፤2ኛ፤4ኛ እና 13ኛ ስር የተዘረዘሩት ይዞታዎች የውርስ አለመሆናቸዉን፣ ሌሎች በክስ የተጠቀሱት የዉርስ ይዞታዎች መሆናቸዉን ጠቅሰዉ እኩል እንድንካፈል ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ግራ ቀኝ በተካካዱት ፍሬ ነገር ላይ ካከራከረ በኋላ በክሱ በተራ ቁጥር 1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ እና 13ኛ ላይ ከተጠቀሱት ይዞታዎች ዉጪ ያሉት ሁሉም ይዞታዎች የሟች የዉርስ ሀብት ናቸዉ በማለት ይህንኑ ወራሾች እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች ቅር በመሰኘት ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በተለይ ባቀረበዉ የይግባኝ ቅሬታ በሥር ፍርድ ቤት በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ ይዞታ የግራ ቀኝ እናት በህይውት በነበሩበት ወቅት ሐምሌ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ተደርጎ በቡራዩ ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት ተመዝግቦ በተረጋገጠ ኑዛዜ ለአሁን አመልካች ተሰጥቶት፣ ኑዛዜዉም ቀርቦ መልስ ሰጭዎች ያልተቃወሙ መሆኑንና በዚህ ይዞታ ላይ የእርቅ ስምምነት ተደርጎ እያለ የስር ፍርድ ቤት የውርስ ንብረት ነው በማለት የወሰነው ትክክል ስላልሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤትም በዚሁ ጉዳይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ በሥር ፍርድ ቤት ለቀረበው ክስ አመልካችን ጨምሮ ሁሉም ተከሳሾች በሰጡት መልስ በ1ኛ ተራ ቁጥር ስር የተገለጸው ይዞታ ሟች በኑዛዜ ለአሁን አመልካች ሰጥታው ሲጠቀምበት እንደነበር እና በ3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተገለፀው የውርስ ሃብት እንደሆነ አምነው የስር ከሳሾች እንዲካፈሉ በጠየቁት መሠረት የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 242 መሠረት ብይን ከሰጠ በኋላ በ3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ ይዞታ በኑዛዜ ለአሁን አመልካች ተሰጥቷል በሚል የስር ተከሳሾች አቤቱታቸዉን በማሻሻል ያቀረቡ ቢሆንም፣ ይዞታዉን አስመልክቶ የተስተካከለ በሌለበት የተሰጠ ብይን ተከሳሾች ባመኑት መሠረት የተሰጠ ነዉ በማለት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካችን ጨምሮ የስር ተጠሪዎች በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የይግባኝ አቤቱታዉን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች ቅሬታዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ ተጠሪዎች የውርስ ይዞታ ነው በማለት በክሱ 3ኛ ተራ ቁጥር ሥር የጠቀሱት ይዞታ ሟች እናታችን በህይወት በነበረችበት ጊዜ በሙሉ ጤንነቷ የሰው ምስክሮችን አስቀምጣ ሐምሌ 09 ቀን 2007 ዓ.ም በቡራዩ ፍትህ ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ባደረገችዉ ኑዛዜ አስተላልፋልኝ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ስጠቀምበት የቆየሁ እና እስካሁንም በእጄ የሚገኝ መሆኑን አስረድቼ እያለሁ የስር ፍ/ቤቶች ባልተገባ መንገድ በመረዳት የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ 1ኛ ተጠሪ የእናታችን ህጋዊ ተወካይ የነበረች ሲሆን በመ.ቁ.67874 በኑዛዜው እና ክስ ውስጥ በ3ኛ ተራ ቁጥር የተገለጸው እንድንለቅላት ከሳን በወቅቱ በሀገር ሽማግሌ አማካይነት ግንቦት 14 ቀን 2010 በተጻፈ የእርቅ ስምምነት አድርገን ስምምነቱም በችሎት ቀርቦ ጸድቆ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ሟች እናታችን በወቅቱ ክስ ማቅረቧ ኑዛዜውን እንዳነሳች በመገመት ውሳኔ መሰጠቱ ግምታዊ እንጂ በማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ ለአመልካች ተላልፏል እንዲሁም በእርቅ ያለቀ ጉዳይ ነዉ በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የታለፈበትን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪዎች መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ መልስ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር አቤቱታዉ ዉድቅ ሆኖ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ሚያዝያ 05 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም፣ ተጠሪዎች በስር

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በዉርስ የሚተላለፉላቸዉ የሚች ይዞታዎች ናቸዉ በማለት ከ1ኛ እስከ 15ኛ ተራ ቁጥር ያሉት ይዞታዎችን በዝርዝር በመጥቀስ ሲሆን፤ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች በሰጡት መልስ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ እና 13ኛ ላይ ከተጠቀሱት ዉጪ በክሱ የተጠቀሱት ሁሉም ይዞታዎች የዉርስ ሀብት መሆናቸዉን ጠቅሰዉ ለወራሾች እንዲከፋፈል መጠየቃቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡ ከዚህም የምንገነዘበዉ በክሱ በ3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ እና አመልካች ለዚህ ሰበር አቤቱታዉ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የዉርስ ይዞታ ስለመሆኑ አመልካች እና የስር ተከሳሽ ያመኑ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ ተከሳሽ የከሳሽን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት በታመነዉ ልክ ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 242 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የስር የወረዳዉ ፍርድ ቤትም በዚሁ መሠረት በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ እና 13ኛ ተራ ቁጥር ላይ ከተጠቀሱት ዉጪ ያሉት ይዞታዎች የዉርስ ይዞታዎች ናቸዉ በማለት ብይን ከሰጠ በኂላ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ እና 13ኛ ላይ ግን የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች ሐምሌ 09 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ ኑዛዜ ተላልፎልኛል በማለት የተከራከረዉ በክሱ በ1ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉን ይዞታ እንጂ በ3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰን ይዞታ አለመሆኑን ነዉ፡፡ ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች ፍርድ ቤቱ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ጨምሮ በተከሳሾች ያልተካዱ ይዞታዎች የዉርስ ይዞታዎች ናቸዉ በሚል ብይን ከሰጠ በኂላ አሻሽለዉ ባቀረቡት መልሳቸዉ ለዚህ ሰበር አቤቲታ ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በኑዛዜ የተላለፈ ነዉ የሚል ክርክር ማንሳታቸዉን ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ ያደረገዉም፣ መልሱ ተሻሽሎ የቀረበዉ በይዞታዉ ላይ ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍትሐብሔር ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለዉ መልኩ ሊመሩ ይገባል፡፡ ክርክሮችን በአጭር ጊዜ፣ ባነሰ ወጪ እና ድካም በመምራት በመጨረሻም በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ መስጠት ነዉ የሚለዉን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉን ዓላማ ማሳካት የሚቻለዉም፣ ክርክሮችን በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ በተመለከቱት ደንቦች እና መርሆዎች መሠረት መምራት ሲቻል ስለመሆኑ እሙን ነዉ፡፡ ክርክሮችን ሥርዓት ባለዉ መልኩ በመምራት ዉሳኔ ላይ ለመድረስ በክርክር ሂደት ፍርድ ቤቶችና ተከራካሪ ወገኖች ሊተገብሯቸዉ የሚገባቸዉም ደንቦች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ የተለያዩ ድንጋጌዎች ተካተዉ እናገኛለን፡፡ ከዚህም ዉስጥ አንዱ የክስና የመልስ አቤቱታ ማሻሻል የሚቻልበትን ሥርዓት አስመልክቶ በህጉ አንቀጽ 91 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤት በእራሱ አነሳሽነት ወይም ከተከራካሪዎች በአንዱ በሚቀርብ ጥያቄ የክስ ወይም የመልስ አቤቱታ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡ አቤቱታ የሚሻሻለዉ ከዉሳኔ በፊት ስለመሆኑም ከድንጋጌዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ክስ ወይም መልስ እንዲሻሻል መፍቀድ ክርክርን ወደ ኂላ የሚመልስ እና በተከራካሪዎች ብሎም በፍርድ ቤቱ ወጪ እና ጊዜ ላይ አሉታዊ ዉጤት የሚስከትል በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቶች አቤቲታ እንዲሻሻል ትዕዛዝ ከመስጠታቸዉ በፊት አቤቱታዉ ተሻሽሎ ካልቀረበ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የማይችል መሆን አለመሆኑን በጥንቃቄ ሊያጤኑ ይገባል፡፡ ከዚህም አልፎ የተከራካሪ ወገኖችን ቅን ልቦና ጭምር ግምት ዉስጥ እንዲያስገባም ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 91 ድንጋጌ ቃል በቃል የተቀዳበት የህንድ አገር የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ትዕዛዝ (order) 6 ደንብ (rule) ቁጥር 17፣ 16 እና 18 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ አቤቱታ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማድረግ ረገድ ፍርድ ቤቶች ከግምት ዉስጥ እንዲያስገቡ የሚጠበቅባቸዉ መመዘኛዎች ምን ምን እንደሆኑ በአገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የዳበረ ሲሆን፣ እንደ መመዘኛም ተወስዶ እየተሰራበት እንደሚገኝ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ከመመዘኛዎቹ ዉስጥም የቅን ልቦናን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከራካሪዉ ወገን ቀደም ሲል ያመነዉን ፍሬ ነገር በመካድ የሚያቀርብ የአቤቱታ ማሻሻያ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም የሚሉ ይገኙበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች፣ መልሳቸዉን በማሻሻል ሰበብ አስቀድሞ አምነዉ የነበረዉን በክሱ 3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተመለከተዉን ይዞታ በመካድ የዉርስ ሳይሆን ለአመልካች በኑዛዜ የተሰጠ ነዉ በማለት የተከራከሩት፣ ይዞታዉ የዉርስ ነዉ በሚል አስቀድሞ ብይን ከተሰጠ በኂላ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ መልሱ ተሻሽሎ የቀረበዉ አከራካሪዉን ይዞታ አስመልክቶ ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ ከመሆኑም በላይ አስቀድሞ ያመኑትን በመካድ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ አመልካች በተሻሻለዉ መልሱ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በቀደመዉ መልሱ ደግሞ አምኖ ስለተከራከረ ይዞታዉ የዉርስ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ጭብጥ ተይዞ አሁን ላይ እያቀረበ ካለዉ ክርክር አንፃር ሊመረመር የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉም አመልካች ቀደም ሲል አምኖ ያቀረበዉንና በዚህም መሠረት ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ እንደገና ክርክራቸዉን በመቀየር ያቀረቡት መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 91 አንፃር ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ በትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡

በመሠረቱ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ፣ ለትዕዛዙ ምክንያት የሆነዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 420555 ላይ ታህሳስ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*